# የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ

# (ቅንጅት) አመራር

# የአሜሪካ ጉብኝት አስተባባሪ ኮሚቴ

# ማብራሪያ

በአሜሪካ የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ከፍተኛ የአመራር አባላት ጉብኝት ማስተባበርን፤ የኢንጅነር ኃይሉ ሻዉልን አቀባበልና የአሰተባባሪ ኮሚቴዉን የሥራ ድርሻ በተመለከተ ባለፈዉ ሳምንት በመገናኛ ብዙሀን የተሰነዘሩትን አሰተያየቶችና መግለጫዎች እንድናጤናቸዉ ተገደናል።

ይህን ማብራሪያ መስጠት ያስፈለገዉ የአስተባባሪ ኮሚቴዉ ባለፉት ሳምንታት የማስተባበር ሥራዉን ከጀመረ አንስቶ የሥራ ድርሻዉንና ተሳትፎዉን በማመልከት የተፈጠረዉን ዉዠንብር ለማሰተካካል ነዉ።

የቅንጅት መሪዎችን አሜሪካ መምጣት ተከትሎ አስተባባሪ ኮሚቴዉ ከተደቀኑበት በርካታ ሰራዎቹ መካከል የተለጠፈብን ስም እና የተፈጠረዉን ዉጥረት ግልፅ ለማድረግ የተሰጠ መግለጫ ነዉ።

የአስተባባሪ ኮሚቴው ሚናና ተሳትፎ፤ የቅንጅት አሜሪካ መሪዎች ጉብኝት አስመልክቶ በአስተባባሪ ኮሚቴው ላይ በአደባባይ የተሰጡትን መግለጫዎች ሰምተን እንዳልሰማን በመሆን ለማለፍ ፈልገን ነበር። የሆነ ሆኖ ባለፉት ቀናት በተደጋጋሚ በመገናኛ ብዙሃን የቀጠሉት ውንጀላዎች ሕዝቡን እያሳሰቡና ዉዠንብርም እየፈጠሩ በመሆኑ በእኛ በኩል ይህን ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አገኘነዉ።

ይህንን ማብራሪያ ለመስጠት በእኛ በኩል ስንወስን እንዲሁ በቀላሉ አልነበረም እንዲያዉም በሀዘን እና በጥንቃቄ በማጥናት የሚፈጠረዉን ስሜት በማጤን ጨምር ነዉ። ይህንን ዉንጀላ መልስ ለመስጠት በርካታ ጉዳዮችን ከግራ ቀኝ ቃኝተናል፤

1. በአሜሪካ ሀገር በጉብኝት ላይ በሚገኙት የተለያዩ ወገኖች መካከል የበለጠ መቋሰልን እንዳይጭርና አለመግባባቱ ወደባሰ ደረጃ እንዳይሸጋገር፤

በድርጅትና በግለሰብ መካከል ያለዉን ጉዳይ ይበልጥ ዉዥንብር ዉስጥ እንዳያስገባዉ፤

4. የእኛ መግልጫ መስጠት አሁን በመራር ሁኔታ ላይ ያሉትን የተለያዩ የመገናኛ ብዙሁን መካከል የበለጠ ዉንዠብር እንዳያስገባ፤
5. በአሜሪካም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች በድርጅታዊ ሂደቱ ያለመግበባቱን ባልተጠበቀ ሁኔታ እንዳያባብሰዉ፤
6. እኛ የምንሰጠዉ መግለጫ በሌሎችና በእኛ መካከል አፍራሽ ዉጤት እንዳያስከትል በማሰብ፤
7. የመጭዉን የእርቀ ሰላም ሂደት እንዳያደናቅፍና መካካሻ መግለጫ እንዳይሆን በመሰጋት፤
8. በአሁኑ ወቅት ያለዉን ድርጅታዊ መቀናቀን ከግምት በማስገባት ወይም አስተዋፅኦ እንዳያደርግ በማለት፤
9. ሕዝብ የእኛን መወንጀል በተዘባ መልኩ እንዳያየዉ ወይም በተዘባ መልኩ እንዳይገነዘበዉ መግለጫ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤
10. እንዲህ አይነቱ ፕሮፖጋንዳ ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብት ጠላቶች ተጨማሪ ጊዜ መሸመቻ እንዳይሆን በመፈለግ ነበር የመግለጫውን መውጣትና አለመውጣት ላይ ያተኮርነው።

በመጨረሻም ይህን በተመጠነ መረጃ ላይ የተመረኮዘን መግለጫ መስጠት አሰፈላጊነቱን በመገንዘብ ወሰንን። ይህ መግለጫ የሚጎረብጣቸዉ ወገኖች ቢኖሩ የሕዝብን በሁሉም ወገን የሚነገረውን የታሪክ መረጃ በማግኘት እዉነቱን እንዲያመዛዝን የማድረግ ሂደት መሆኑን ልንገልጽ እንወዳለን።እንደዚሁም ሌሎች እንዲከተሉት የምንመክረዉን በሀላፊነት የተጠያቂነት ድርሻ መወጣት ግዴታችን መሆኑን በማጤን፤ በዚህ ረገድ በዉጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሀን ይህንን የተጠያቂነት ድርሻ እንድንወጣ ለተጫወቱት ሚና ማመስገን እንወዳለን።

ይህ መግለጫችን በተመጠነ መረጃ ላይ በመመርኮዝ የድርጊቶችን ቅደም ተከተል በመጠበቅ የቀረበ ነዉ። ይኸዉም በተወሰኑ መረጃ ፋይሎች ላይ በመመርኮዝ የተከናወኑ ተግበራትንና ሂደቶችን ያመለክታል። የዚህ መግለጫ ዋና ግብ አግባብ ያልሆነ ወይም ያልተጠበቀ አላማ ወይም መጥፎ ግምት ለማንም ለመስጠት አይደለም። ዋናዉ የመግለጫችን አላማ በእኛ በኩል በልኡካን ቡድኑ መምጣት የተከናወኑ ተግባራትና የደረሱ መረጃዎችን በማቅረብ አንባቢዎች የራሳቸዉን ነፃ የሆነ መደምደሚያ ይደርሳሉ ከሚል እምነት ነዉ።

# የተከናወኑ ተግባራት በቅደም ተከተል

በነሀሴ 17ቀን 2007 እኤአ ለመጀመሪያ ጊዜ ባወጣነዉ መግለጫ የቅንጅት ልዑካን ቡድን አባላት ይመጣሉ። እነርሱም አቶ ኃይሉ ሻውል ሊቀመንበር፤ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ም/ሊቀመንበር፤ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ የአ.አ ከተማ ተመራጭ ከንቲባና አባል፤ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ቃል አቀባይ አቶ ብሩክ ከበደ እና አቶ ግዛቸዉ ሽፈራዉ ሲሆኑ ልዑካኑ በነሀሴ 29ቀን 2007 ይመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል የሚል ነዉ።

በሁለተኛዉ ነሀሴ 24 ቀን 2007 መግለጫችን ደግሞ በአሜሪካ ኤምባሲ የመግቢያ ፍቃድ (ቪዛ) በወቅቱ አለመጠናቀቁ የተነሳ የነሀሴ 29ቀን 2007 የጉብኝት መርሀ ግብር ሊዘገይ እንደሚችል ገልጸናል። በዚሁ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ወደ አሜሪካ በሚመጣዉ የልዑካን ቡድን ጋር አቶ ኃይሉ ሻውል የቅንጅት ሊቀመንበር ፤ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ም/ሊቀመንበር፤ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ የአ.አ ከተማ ተመራጭ ከንቲባና አባል ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ቃል አቀባይ ፤አቶ ብሩክ ከበደ አቶ ግዛቸዉ ሽፈራዉ እንደሚመጡ አስታዉቀናል።

በ3ኛዉ ጋዜጣ መግለጫ በመስከረም 5ቀን 2007 ደግሞ የቅንጅት አመራር ልዑካን ቡድን በመስከረም 9 ቀን አሜሪካ ይገባል። ቡድኑ ወ/ት ብርቱካን መደቅሳ ም/ሊቀመንበር፤ ዶ/ር ኃይሉ አረአያ ቃል አቀባይ ፤አቶ ብሩክ ከበደ እና አቶ ግዛቸዉ ሽፈራዉን እንደሚይዝ አስታዉቀናል።

ከዚህም ሌላ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ የአ.አ ከተማ ተመራጭ ከንቲባ ቀደም ብለዉ አሜሪካ በግል ጉዳይ የገቡ መሆኑንና ቡድኑን እንደሚቀላቀሉ በመስከረም 5 ቀንጋዜጣዊ መግለጫ ላይ በተለየ የገለጽነዉ "የቅንጅት ሊቀመንበር አቶ ኃይለ ሻውል ከቡድኑ ጋር እንደማይመጡ ይህ መግለጫ እስከተሰጠ ድረስ ከአሜሪካ የመግቢያ ፈቀድ አቶ ኃይሉ አለማግኘታቸውን እንዲሁም በአሁኑ ወቅት የመግቢያ ፈቃድ ቢያገኙም እንኳ የአሜሪካዉን የልዑካን ቡድን ሊቀላቀሉ አይችሉም።ይኸዉም በጤንነት ችግር የተነሳ የህክምና ክትትል ያስፈልጋቸዋል" በተጨማሪ የገለፅ ነዉ። "የልዑካን ቡድኑ አቶ ኃይሉ ከገጠማቸዉ የጤና መታወክ በፍጥነት አገግመዉ የልዑካን ቡድኑን በአሜሪካ ሀገር ይቀላቀሉታል የሚል ተስፋ አለዉ"።

በመስከረም 5 ቀን 2007 ይመጣሉ ተብሎ የተነገረላቸው የልዑካን ቡድን አባላት በተያዘላቸው እቅድ መሠረት መስከረም 9 ቀን 2007 አሜሪካ ገቡ። በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈ ኢ-ሜይል ጳጉሜ 3 ቀን 1999 ዓ ም መስከረም 8 ቀን እና 11 በካርቦን ኮፒ ለቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴዎች በዋሽንግተንና በቶሮንቶ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል እንደገለፁት "ወደ አሜሪካ የሚደረገው ጉዞ ጥያቄዎች ማስነሳቱንና በጤና ችግርና በመግቢያ ፈቃድ መዘግየት የተነሳ ወደ አሜሪካ መጓዙን ጉዳይ ሀሳባቸውን መቀየራቸውን ነገር ግን በደጋፊዎች ጠንካራ ጥያቄ የተነሳ እንደገና አሜሪካ ለመምጣትና በሕዝቡ መካከል የተነሱ ጥያቄዎችንና አለመግባትን መፍትሄ ለመስጠት መገኘት ያስፈለጋቸው መሆኑን በመጥቀስ አሜሪካ ሀገር ረቡ መስከረም 1 ቀን 2000 ከሰዓት በኃላ እንደሚገቡ እና የህክምና ክትትል እንደሚያደርጉና አርብ መስከረም 3 ቀን 2000 ዋሽንግተን ዲሲ እንደሚገቡ ቅዳሜ በተያዘው መርሀ ግብር ለመሳተፍ ዝግጁ መሆናቸውንና በእኛ በኩል የተያዘው እቅድ እርሳቸውን እንደሚያሳትፍ እንዲገለጽላቸው ጠይቀዋል"

በመስከረም 10 ቀን 2007 ለኢንጅነር ኃይሉ ሻውል በሰጠነው መልስ የጳጉሜ 3 ቀን 1999 የኢሜል መልክት መሠረት ፈቃደኛ መሆናችን በመግለጽ "በመጨረሻ የጋዜጣዊ መግለጫችን ላይ የጤናወትን ይዞታ እና በአሜሪካ ኤምባሲ የቪዛ መዘግየቱን አስመልክተን ለህዝብ ገልጸፀናል። አሁንም የዘገየ ቢሆንም ቅሉ መግቢያ ፈቃድ

በማግኘትዎ በጣም ደስተኞች ነን። ከሁሉም በላይ ደግሞ የጤንነትዎ ችግር አፋጣኝ ትኩረት ቢሻም ቅሉ ለመምጣት መወሰንዎና የልዑካን ቡድኑን መጀመሪያ በታቀደለት መሰረት እርስዎ ለመገኘት መወሰንዎ የበለጠ ደስታ ሰጥቶናል "።

" በጣም በጉጉትና በደስታ ብዙሃኑ አሜሪካ- ኢትዮጵያውያን የእርስዎን መምጣት እየተጠባበቅን ነው። አቀባበልንም በተመለከተ የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነን።"

"የሚያወጧቸውን መመሪያዎች በልዑካኑ ቡድኑ በኩል ቢያሳውቁን የድጋፍ ሰጭ ኃይሎችንና ግለሰቦችን ለማስተባበር ብሎም በስራ ላይ ያሉትን እቅዶች ለማከናውን ይበልጥ ይረዳናል።ከጉዞውት በፊት ወይም በጉብኝት ጊዜ ፍላጎትዎንና ምኞትወን መከናዎን የሚገባቸውን ሥራዎች በልዑካኑ በኩል እንዲያሳውቁን በትህትና እንጠይቃለን መመሪያዎ ለልዑካኑ እንደደረሰ ጉዳዩን ከግቡ ለማድረስ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን"

ኢንጅነር ኃይሉ በመስከረም 10 ቀን 2007 በአማርኛ በላኩት የኢሜይል መልእክት ቀደም ብለን የላክንላቸው መልዕክት እንደደረሳቸው በማሳወቅ ቅንጅትን ለማጠናከር በሚደረግ እንቅስቃሴዎች መሣተፍ እንደሚፈልጉ ገልፀው ያወጣናቸው መርሃ ግብሮች በአስቸኳይ ቢላክላቸው በጉዳዩ ተሳታፊ መሆናቸውን የበለጠ ሊያረጋግጡልን እንደሚችሉ ገልፀውልናል።

በመስከረም 11 ቀን 2007 ለኢንጅነር ኃይሉ በላክነው ምላሽ የሚከተለውን ገልፀናል "አርቅቀን ለልኡካን ቡድኑ ባቀረብነው ዝርዝር ፕሮግራም የእያንዳንዱ ልዑክ የሥራ ድርሻ ሚና አልታተተም። የታቀደው የአስተባባሪ ኮሚቴው ዝግጅቶችን በማቀናበርና በማመቻቸት እንዲያገለግል የዝግጅቱ አቀራረብ ደግሞ እንደየአስፈላጊነቱ ከአባላት ጋር በመመካከር ልዑካኑ እንዲወስን። እነዚህ ሥራዎች ሙሉ በሙሉ ለልዑካን ቡድኑ የተተው ሲሆን በአፈፃፀማቸውም ላይ የምንሰጠው አገልግሎት የለም። በተጨማሪም በመጨረሻ የኢሜል መልእክትዎ የጠየቁትን የልዑካን ቡድኑ እንዲያጤነውና በቀጥታም ምላሽ እንዲሰጥበት መልእክቱን ለልኡካኑ አስተላልፈናል። እንዲሁም የአስተባባሪ ኮሚቴው የሚያስተናግዳቸው ጉዳዩች ጥንቃቄ የሚሹ መሆናቸውን ለማሳሰብ "የአስተባባሪ ኮሚቴ ሆነን በመስራታችን እንደሚደሰቱ ተስፋ አለን በተወሰኑ ስራዎች ዙሪያ በተለይም ልዑካኑ እዚህ ከደረሰ ጊዜ ጀምሮ ከልዑካኑ በሚቀርብልን ጥያቄ መሠረተ ዕርዳታችንና ትብብራችን ይቀጥላል። መደረግ ባለባቸው ሥራዎች ላይ አስተያየታችንን እናቀርባለን ሆኖም ግን ሀሳቡን የመቀበል ወይም አለመቀበል በአጀንዳ ማካተተት ወይንም አለማካተት የልዑካኑ ኃላፊነት ነው።" ኢንጅነር ኃይሉ በጳጉሜ 6 ቀን 1999 (መስከረም 11) በአማርኛ በተፃፈ የኢሜል መልእክት መልክታችን እንደደረሳቸው በመጥቀስ በመስከረም 15 በ4:30 እንደሚደርሱ አሳውቀውን ፕሮግራማቸውም ቅዳሜ የግል ውይይት እሁድ ከድጋፍ ሰጭ ክፍሎችጋር ውይይት ሰኞ ደግሞ የግል ፕሮግራም።

የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላችን አቶ ታማኝ ቀደም ብሎ በተያዘ ዕቅድ ምክንያት በመስከረም 13 2007 ወደ ጀርመን ሄዶ ዋሸንግተን በመስከረም 16 ተመልሷል።

እነደዚሁም ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረ ማርያም ዲሲ ውስጥ ከሳምንት ቆይታ በሁዋላ ሲያትል ውስጥ በመስከረም 16 ለማድረግ ቀደም ብሎ ለታቀደው የሚሊኒየም አከባበር ላይ ዝግጅት ለማድረግ ወደ መኖሪያ ቦታው ሄደዋል።

በመስከረም 15 2007 ኢንጅነር ኃይሉ ዋሽንግተን ደረሱ በመስከረረም 15 ቀን በዋሽንግተን ዲሲ ሜትሮ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ዶር ሰለሞን አለሙ ሬጋን አውሮፕላን ማረፊያ በኢንጅነር ኃይሉ አቀባበል ላይ ተገኝተው ነበር

ከኢንጅነር ኃይሉ ጋር ያለውን የግንኙነት ሁኔታ በተመለከተ በነሐሴ 8እና 11 ቀን 2007 የአቀባበል ኮሚቴ አባላት ቀጥተኛ ግንኙነት አድርገን ቀዳሚዊ መመሪያውን መሠረት በማድረግ ሁሉንም ወገን ያካተተ የጉብኝት መርሀግብር ለማዘጋጀት ሞክረናል አስተባባሪ ኮሚቴው በኢንጅነር ኃይሉ ሀሳብ መሠረት የተለያዩ ግለሰቦችን ቡድኖችን ያካተተ ለማድረግ ብርቱና ጥልቀት ያለው ተግባር አካሂደናል።

በመስከረም 5 ቀን 2007 በወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ የአስተባባሪ ኮሚቴው የገለጸው "አስተባባሪ ኮሚቴው ከቅንጅት ከፍተኛ አመራር በተሰጠዉ መመሪያ መሰረት ፈቃደኛ ከሆኑ የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ቡድኖች ጋር በመቀራረብ ሲሰራ ቆይቷል። እንደዚሁም የልዑካኑ ቡድን ተልእኮ የተሰካ እንዲሆን ሁሉም የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ወገኖች ተሳትፏቸውን እንዲቀጥሉ ያበረታታል ድጋፋቸዉንም በደስታ ይቀበላል። አስተባባሪ ኮሚቴዉ ለቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ቡድኖችና አባሎቻቸው ላደረጉት የገንዘብና ለዝግጅቱ ለሰጡት ድጋፍ ታላቅ ምስጋና ያቀርባል።የድጋፍ ሰጭ ቡድኖች ከአስተባባሪ ኮሚቴው ጋር አብረው ለመሥራት ለሚፈልጉ ሁሉ ይህንኑ አጠናክረዉ እንዲቀጥሉ ፍላጎቱ መሆኑን በትህትና ይገልጻል"።የልዑካን ቡድኑ ከመምጣቱ ሶስት ሳምንታት በፊት የአስተባባሪ ኮሚቴው አንድ ጊዜ ረዘም ላለ ሰአት እንዲሁም ሁለት ጊዜ ደግሞ ለአጭር ደቂቃዎች ከኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ጋር ተነጋግረናል።ከዚህም በላይ በተደጋጋሚ በስልክ ለማግኘት ያደረግናቸው ጥሪዎች ሁሉ አልተሳኩም ።የስልክ ጥሪያችን መኖሪያ ቤታቸው ጭምር ሞከርን ነገር ግን በህክምና ምክንያት ይሁን በሌላ ሁኔታ የስልክ ጥሪያችን ሊሳካ አልቻለም።

ቀደም ሲል እንደገለጸነው በኢንጅነር ኃይሉና በእኛ መካከል በርካታ የኢሜል ልውውጦች ተደርገዋል።ከዚህ ላይ መታወቅ ያለበት የአስተባባሪው ኮሚቴ ድርሻ አንዱ ዋና ተግባር የድጋፍ ሰጭ ቡድኖችን ከልዑካን ቡድኑ ጋር የተሳካ ተግባር እንዲያከናውኑ ማስተባበር ነው።በዚህ ረገድ የአስተባባሪ ኮሚቴው ይህንኑ ለማስተባበር ከድጋፍ ሰጭ ቡድኖች ጋር በርካታ ሰአታት አሳልፏል።ነገር ግን አስተባባሪ ኮሚቴውን ሕዝቡ ለልዑካን ቡድኑ እንደ መንገድ አመልካች አድርጎ የማየት የተሳሳተ አመለካከት አለ።ይህ አስተሳሰብ በፍጹም ትክክል አይደለም።ለማረጋገጥ ያህል የልዑካን ቡድኑ አሜሪካን እንዲጎበኝ ያስቻሉት የድጋፍ ሰጭ ቡድኖች ናቸው።የድጋፍ ቡድኖቹ የሰው ኃይል በመመደብ ፤የገንዘብ አስተዋጽዖ በማድረግና ጊዜአቸውን ጭምር በመስጠት የልዑኩ ቡድን ዝግጅት ሙሉ በሙሉ ሀላፊነቱ የእነርሱ ነው ለዚህም ተግባር ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል።

እዚህ ላይ ሁለቱ የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት በመስከረም 15 ቀን በነበረው አቀባበል

አለመገኘት የፈጠረውን ሁኔታ አስመልክቶ ሁሉም ሊረዳ የሚችለው ሁለታችንም የኮሚቴው አባላት ሌሎች የሙያና የማህበራዊ ተሳትፎዎች ያሉብን መሆኑን እንዲረዱልን እንፈልጋለን።በዚህ ረገድ የጊዜ ፤የሰው ኃይል እንደዚሁም ለሌሎች ተግባራት ለማከናወን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የመጓዝ ሁኔታ የገጠመን መሆኑን ሊገነዘቡልን ይገባል።

የአስተባባሪ ኮሚቴው የልዑካን ቡድኑን አጅቦ ከቦታ ቦታ የመጓዝ እቅድ የለውም አልነበረውምም።የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ይህንን ጉዳይ በማስተባበር ረገድ የሚጠይቀውን ወጭ የምንሸፍነው ከራሳችን የግል ገንዘብ ነው።ከሌላ ግለሰብ ፤ተቋም ወይም ድርጅት የገንዘብም ሆነ ሌላ ማካካሻ አልተሰጠንም አላገኘንም።

የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ድርጅት አባል አይደለንም።በዚህ ረገድ አሁን እያከናወን ያለነው ተግባር በፓሪቲዎቹ በቀረበልን ጥያቄ መሰረት ነው።በዚህም የምንሳተፈው ብቸኛው ፍላጎታችን በኢትዮጵያ ዴሞክራሲን፤ነጻነትንና ሰብአዊ መብት ለማስከበር በሚደረገው ትግል አስተዋጽዖ ለማድረግ ነው።

የአስተባባሪ ኮሚቴው በአሁኑ ወቅት በሚከናወኑ ተግባራት ምንም አይነት ወገናዊነት የለንም ገለልተኞች ነን፤

የአስተባባሪ ኮሚቴው በማንኛቸውም ወገኖች የሚሰጡ አስተያየቶችን በማነጣጠር እርምጃ አይወስድም፤

የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት የጉብኝት አሰራራችን ያልተደሰቱ ካሉ በግልጽ ይቅርታ ለመጠየቅ ዝግጁ ነን፤

የአስተባባሪ ኮሚቴው ሁሉንም የቅንጅት መሪዎች በእኩል ለማገልገል ዝግጁ ነን፤

የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ይህንን መግለጫ በበጎ ፈቃደኞች አስተርጉመን በአማርኛ ይቀርባል፤

የአስተባባሪ ኮሚቴው የቅንጅት መሪዎች የሰሜን አሜሪካ ጉብኝት የተሳካ እንዲሆን አስተዋጽዖ ላደረጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ከፍተኛ ምስጋናችንን ለሁሉም እናቀርባለን፤

**በዚህ ጉዳይ ላይ ይህ መግለጫ በጽሁፍም ይሁን በሌላ መንገድ ለመግለጽ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ይሆናል።**

**ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማሪያም**

**አቶ ታማኝ በየነ**

**ዶክተር ሰሎሞን ዓለሙ**